# " የሦስት ትውልድ እንባ "

## የጎንቻው

ሃሌ ለጋዋ አለቀሰች ተንሰቅስቃ፤
ብርቱ እናቷን ከእቅፏ ተነጥቃ፤
አቅፋ-ስማ ሳትጠግባት፤ተሞልቅቃ፤
ተገፍትራ ስትወጣ ተመንጭቃ፤
በእስር ቤት አጥር አሹልቃ፤
በእናቷ ህመም አሳር ተጨንቃ፤
ማልቀስ እንጅ በእንባ ጸበል ተጠምቃ፤
በትውልድ አባዜ ልጅነቷን ተነፋጋ ናፍቃ፤
በየሰንበቱ ለእናቷ መክለፍት ሰንቃ፤
ጨዋታ አትሻ በእስር ቤት ሰልፍ ስትንቃቃ፤
የዋኋ ሃሌ ምን ክፋትስ አሳር አውቃ፤
የትውልድ ደም-እንባ አፍሶ የማያበቃ።

አምሳለ ኢትዮጵያ ብርቱ እናቷ ታስራ፤
ወልዳ እንዳታሳድግ ዜጋ እንዳታፈራ፤
እንዳታይ አዛውንት እናት አባት ጡራ፤
ለፍትህ እንዳትቆም አገር እንዳትመራ፤
አሳር ሕመም ሆናት ሲያል ተውርውራ፤
በጨለማ አኖሯት አይኗ እንዳያበራ፤
የአበሻዋን ኩራዝ ነፀብራቋን ጮራ፤
ፀሃይዋን ጋረዱን የምስራቋን አውራ፤
ብሌኗ ሳትጠፋ ብልጭታዋ ኖራ፤
ጨለማ እንዳይውጠን ሞረሽ ተጠራራ፤
ችቦ እንቀባበል እንለኩስ ደመራ፤
ቀን እንዲወጣልን ደምቆ የሚበራ።

እማሆይ አልቅሰው ሆዳቸው ቆሰለ፤
የእናት ማህፀናቸው እየተማለለ፤
ወልደው ያምጣሉ ግልግል የታለ፤
አዝነው ቢማጸኑ ቢማልዱ አበለ፤
በር አጥሩ ተዘጋ ከንቱ ሰሚ የለ፤
ኤሉሄ! ይላሉ አገር ወገን ካለ።

ደም እንባ አለቀሰች፡ሲቃ ተናንቋት፤
የእስር ቤቱ ደዌ በሽታው ጎድቷት፤
ከአገር - ከዘመዱም  ጠያቂ ነስቷት፤
ታማለች በጠና ስቃይ በዛባት፤
የልጅ የእናቷ እንባ ሰቀቀን ሆኗት፤
ብርቱዋ ደክማለች ግፉ ጸንቶባት።

መንፈሷን ከአወከው መዳኛም የላት፤
ያ ክፉ ቦታ ነው ነፍሰ-በላ ቤት፤
የመለስ መግደያ በእስር-ጥላ ሞት፤
'እስራትን' የቀማን ቀድሞ እንዳይሻት፤
እንድረስ በነፍሷ ወገን ይሁናት።

የእንባ ጎርፍ ይወርዳል የትውልድ ብሶት፤
ገኘሮዎች ገድበው የሚዋኙበት፤የሚያጠልቁበት፤
ወይጦ-ባህራቸው፤ምድረ-ገሃነሙ 'ቃሊቲ' ግዞት፤
የሶስት ትውልድ እንባ የሚያቂትበት፤
ሃያ ዘመን ለቅሶ ያላባራበት፤
የደም መተተኞች የሚያቂሩበት፤
አስጋሪዎች ይግቡ ደፍቀው ይጥገቡት፤
ወገን በአገር ይምከር በውጭ ይሚገት፤
አገር ነፃ ይውጣ በምርጫው ዘበት።

የጎንቻው!
yegonchaw@yahoo.co.uk

ማስተዋሻ፤

- ❖ በቅድሚያ ይህችን እንድጫጭር አስጨንቆ ለአነሳሳኝ የውድ እህታችንን የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን እጅግ አሳሳቢ ጤንነት ጉዳይ አምላክ ምህረቱን እንዲልክላትና ለብርቅዬ ልጅዋና ለደካማ እናቷም ለወ/ሮ አልማዝም የአካልና የመንፈስ ጥንካሬ እንዲያገኙ በጸሎት እንድናስባቸው፤

- ❖ እንዲሁም በብዙ ሺህ ለሚቆጠሩ በጨለማ ክፍል፤ በየጫካው፤በየዋሻው በጭካኔ ለታሰሩ፤ለታጎሩ ሁሉ የተስፉ ጎህ እንዲቀድላቸው፤የግፍ ዘመን በቃቹህ እንዲላቸው፤

- ❖ በመጨረሻም ለገዥው ቡድን በኃይልና በትቢዕት ጨዋውንና ታጋሹን የኢትዮጵያን ሕዝብ አስረው፤ ገድለው፤ ገርፈውና ክብሩን ቀምተው ወደ ሃያ ዘመን በስልጣን ላይ ለተፈናጠጡትም ቢሆን አምላክ ልቦናቸውን እንዲያራራውና፤ ቅን እንዲያሳስባቸው፤ፍቅረ ሰላም ይወርድ ዘንድ ምህረት እንዲሸቱ፤

  - ▪ አሻፈረኝ ብለው በጥፋትና በኃል ልማዳቸው ከቀጠሉ ደግሞ አምላክ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ኃይሉን፤ወኔውንና አንድነቱን መልሶለት የዘለዓለም ነፃነቱን በቅርቡ፤እንዲያቀናጀው ጸሎታችንና ትጋታችን ይሁን።